**መሠናዘሪያ:-** ሊጨምሩት የሚፈልጉት ካለ::

**አቶ ብርሃኑ:-** በኔ በኩል ያለኝ አስተያየት መጀመሪያ ጋዜጣው ሚዛናዊ ለማድረግ ኃላፊነት በመውሰዱ አደንቃለሁ:: ሁለተኛ በተለያየ ጋዜጣ ላይ የሚወጡትም ቃለ ምልልሶች ስሜን ለማጥፋት ነው፤ ስለሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ:: የክፋ ህዝብ ደግሞ ይሄን ጠንቅቆ ያውቃል:: ምንም እንኳ እኔቸው ያን አካባቢ ሄደው ማየት ባይችሉም በህዝቡ ተቃውሞ ነው መሄድ የማይችሉት፤ቢሄዱም ምን እንደሚገጥማቸው ያውቃሉ:: የክፋ ህዝብ በብርሃኑ ላይ ቅሬታ አለው ብለው የሚያነሱት በዚህ መልኩ ፍፁም ሀሠት ነው:: ይሄን በድርጅት መዋቅራችን ፈትሸን አንድም ነገር የተገኘ የለም:: ይሄን የፈጠራ ክሳቸውን ቢያቆሙ መልካም ነው:: ነገሩ ከገደብ ስላለፈ መብቴን ለማስከበር ወደ ህግ እንደምሄድ በግልፅ እንድታሠፍሩ እፈልጋለሁ:: አመሰግናለሁ::